ስለሆነም አመልካችና ተጠሪ ቤቱን በግልጽ ሀራጅ በሚያወጣው ዋጋ መሠረት ለማስቀረት የሚስማሙ ከሆነ በስምምነታቸው መሠረት መፈፀም አለበት፡፡ አመልካች እና ተጠሪ የማይስማሙ ከሆነ ግን ቤቱ በግልጽ ሐራጅ ተሸጦ የሟች ወራሽ የሆኑት ሶስት ልጆች ግማሹን ለሶስት እኩል እንዲካፈሉ፣ ተጠሪ ደግሞ የቤቱን ግማሽ ዋጋ እንድትወስድ መደረግ ይገባዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ባቀረበችው ክስ መሠረት በክርክሩ ፊት ሆና እያለ ከተጠሪ ጋር ዳኝነት በጋራ እንድትከፍል የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ህዳር 27 ቀን 1993 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 5436 ሚያዚያ 3 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. አመልካችና ተጠሪ የሚቻል ከሆነ ቤቱንና ቦታውን በአይነት እንዲከፋፈሉ ቤቱን በአይነት ለመከፋፈል የማይችሉ ከሆነ በግልጽ ጨረታ በሀራጅ ተሸጦ ግማሹን ተጠሪ እንዲወስዱ፣ ግማሹን የሟች አቶ ወንድሙ ወራሾች ለሶስት እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስነናል፡፡
4. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ወጭ ተጠሪ ብቻዋን መሸፈን አለባት ብለናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰ/መ/ቁ. 30158

ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካቾች፡-** እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ አደም ሞግዚት ሐይሉ ሲሳይ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** የኮ/ል እሸቱ ተስፋዬ ወራሾች ጠበቃ ወርቅዬ አባይነህ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 83/90 መጋቢት 17 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍታብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 04711 ጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍታብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 255/1999 ጥር 22 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ እናቴ ወ/ሮ አበበች ጀግሬና አክስቴ በየነች ጌቶ አሁን በህይወት የሉም፡፡ እናቴና አክስቴ ከሟች እናታቸው ወ/ሮ ጀማነሽ አቡዬ በውርስ የተላለፈላቸውንና በደሴ መዝገበ ማርያም የስንዴ ግብር እየከፈሉ ይዘውት የቆዩትን በደሴ ከተማ ቀበሌ 05 ቁጥሩ 407 የሆነ ቤትና 668 ካሬ ሜትር ቦታ አቶ በዛብህ ጉሽ አላግባብ የያዘና በስሙ ያዛወረ ስለሆነ ከውርስ ንብረቱ የሚደርሰኝን ብር 6000 (ስድስት ሺህ ብር ) እንዲከፍል

ይወሰንልኝ በማለት የወራሽነት ክስ በማቅረቡ ነው፡፡ አመልካቾቹ በክሱ የተገለፀው ቤትና ቦታ የአቶ በዛብህ ጐሽ የግል ንብረት እንደሆነና ይኸም በደሴ ማዘጋጃ ቤት እንደተመዘገበ ገልፀው የተከራሩ ሲሆን ንብረቱ ያልተከፍፈለ የውርስ ንብረት ነው ቢባል እንኳን የከሳሽ(ተጠሪ) ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካቾች በኩል የቀረበውን ክርክር አልፈው ተጠሪ ያቀረበውን የሰው ማስረጃ መሰረት ንብረቱ የውርስ ንብረት ስለሆነ አመልካቾች ለተጠሪ እንዲያካፍሉ በማለት ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የህግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ይኸ ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት በደሴ ከተማ ቀበሌ 05 ቁጥሩ 407 የሆነው መኖሪያ ቤት ጥንት ለመዝገበ ምህረት ማሪያም የስንዴ ግብር ተገብሮበት ነበር በማለት ቤተክርስቲያን በፃፈው ቀላጤ መነሻ ለሰላሣ ሁለት ዓመት በስማቸው ያለውን ንብረት አካፍሉ መባላችን መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ንብረቱ በአመልካች ባለቤትና አውራሾች በዛብሕ ጐሽ ስም ስለሆነ ተጠሪዎች ሊጠየቁ ይችላሉ የሚለው ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ንብረቱ በውርስ ከወ/ሮ ጀማነሽ አቦዬ በውርስ የተላለፍ ነው፡፡ የተጠሪ እናትና አክስት ይኖሩ ነበር ተጠሪ አውራሽ እናታቸው 1989 ዓ.ም ሞተው በ1989 ዓ.ም የወራሽነት ጥያቄ ያቀረቡ ስለሆነ የይርጋ የጊዜ ገደብ አልተላለፈም፡፡ ንብረቱ የሟች ወ/ሮ ጀማነሽ አቦዬ ስለሆነና ለተጠሪ እናትና አክስት በውርስ የተላለፈ በመሆኑ ተጠሪ ድርሻ መጠየቃቸው ህጋዊ ነው የሚል መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የአመልካችንና የተጠሪን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ ይህ ችሎት ግራ ቀኙ የአከራካሪውን ቤት ባለቤትነት አስመልክቶ ያቀረቡት ክርክር ከመታየቱ በፊት የተጠሪ ክስ በይርጋ የጊዜ ገደብ ይታገዳል ወይስ አይታገድም? የሚለውን ጭብጥ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ተጠሪ ለደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት አስቀርቦ ካሰማቸው እና ፍርድ ቤቱ በውሣኔው ላይ የምስክርነት ቃላቸው ከመዘገበው አንደኛ ምስክር ለመረዳት የሚቻለው የተጠሪ እናት እና አክስት አውራሽ ናቸው የተባሉት ወ/ሮ ጀማነሽ አቡዬ የሞቱት በ1949 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ተጠሪ ባቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ከዚህ በኋላ የተጠሪ እናት ወ/ሮ አበበች ጀግሬና አክስታቸው ወ/ሮ በየነች ጌቶ የእናታቸው የውርስ ንብረት እንዲከፈልና ድርሻቸው በስማቸው እንዲዞር ያቀረቡት ክስ የለም፡፡ ንብረቱንም በስማቸው አላዞሩም፡፡ በተቃራኒው የአንደኛ አመልካች ባለቤትና የሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች አባት አቶ በዛብህ ጐሽ የቤቱን ስመ ንብረት በስማቸው አዛውረውና በደሴ ማዘጋጃ ቤት የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ አስመዝግበው እንደኖሩ ተረጋጋጧል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪው ክስ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000(2) የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚታገድ አይደለም የሚል ብይን የሰጡት ንብረቱ ከዘር የወረደ ርስት ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 (2) “ሟች ከሞተበት ወይም ተከሳሹ በመብቱ ለመምራት ከቻለበት ቀን አንስቶ አስራ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በስተቀር የውርስ ጥያቄ ክስ በማናቸውም አስተያየት ቢሆንም ተቀባይነት አያገኝም” በማለት ይደነግጋል፡፡

ከዚህም ድንጋጌ የምንረዳው ሟች ከሞተ ከአስራ አምስት አመት በኋላ ወይም ተከሳሹ በመብቱ ሊሰራበት ከቻለበት ቀን አንስቶ ለምሣሌ ህፃን ልጅ ወራሽ ሲሆንና ሞግዚትና አስተዳዳሪው መብቱን በአግባቡ ያልጠየቀለት ቢሆን አካለ መጠን ከደረሰበትና በመብቱ ሊሰራበት ከቻለበት ቀን አንስቶ

በአስራ አምስት አመት ውስጥ ክስ ካላቀረበ ጉዳዩ በይርጋ እንደሚታገድ በመርህ ደረጃ ይደነግጓል፡፡ ድንጋጌው ከላይ የተገለፀው የአስራ አምስት ዓመት ጊዜ ሣያልፍ የወራሽነት ጥያቄ ክስ ያላቀረበ ሰው ከአስራ አምስት ዓመት በኂላ ክስ እንዲያቀርብ የሚፈቅደው በአንድ ልዩ ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም ንብረቱ ከዘር የወረደ ርስት ሆኖ ሲገኝ በአስራ አምስት አመት የይርጋ ጊዜ የማይገደብ መሆኑን በልዩ ሁኔታ የደነገገ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ክስ ማቅረብ የሚችሉት ክርክር የተነሣበት ንብረት ከዘር የወረደ ርስት ከሆነ ብቻ በመሆኑ ክርክር የተነሣበት "ከዘር የወረደ ርስት" ምን አይነት ንብረትን ያጠቃልላል? በተለይም ከዘር የወረደ ርስት የሚባለው ቤትን ያጠቃልላል ወይ? የሚለውን ትርጉም መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም "ርስት" የሚለውን ቃል ስንመለከት "ቤተዘመድ የሆነ እያረሰ የሚጠቀምበት ለተወላጅ በውርስ የሚተላለፍ መሬት" ማለት እንደሆነ ከአማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 (2) "ከዘር የወረደ ርስት" የሚለው አገላለጽ፣ ለተወላጅ በውርስ የተላለፈ መሬትን ብቻ የሚመለከት  እንጂ ቤትንና ሌሎች የማይንቀሣቀሱ ንብረቶችን የሚመለከት አይደለም፡፡ መሬት የመንግስትና የህዝብ በመሆኑና አሁን ባለው ህገመንግስታዊ ሥርዓት የመሬት ባለቤት የኢትዮጵያ ብሔር በሔረሰቦችና ህዝቦች እና መንግስት እንደሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ "ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በስተቀር" የሚለው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 (2) ድንጋጌ በአሁኑ ሰዓት የተሻረና ተፈፃሚነት የሌለው ነው፡፡

ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ ርስት የሌለ በመሆኑ ሟች ከሞተበት ወይም ተከሳሹ በመብቱ ሊሰራበት ከቻለበት ጊዜ ጀምሮ ከአስራ አምስት ዓመት በኂላ የሚቀርብና በይርጋ የማይገደብ የወራሽነት ጥያቄ የለም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ እናትና አክስት አውራሻቸው ወ/ሮ ጀማነሽ አቦዬ ከሞቱበት 1949 ዓ.ም ጀምሮ የወራሽነት ክስ ያላቀረቡ በመሆናቸው ይርጋው መቆጠር ያለበት



ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር የተጠሪ አውራሽ ወ/ሮ አበበች ጀግሬም ሆኑ ተጠሪ አውራሻቸው ከሞቱ ከሰላሣ ዘጠኝ አመት በኂላ ተጠሪ የወራሽነት ጥያቄ ያቀረቡ በመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 (2) በተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ክሳቸው ቀሪ ይሆናል፡፡ የተጠሪ እናት እቤቱ ውስጥ መኖራቸው የውረሱን ንብረት የተካፈሉና በስማቸው ያደረጉት መሆኑን አያረጋጋጥም፡፡ ስለሆነም የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤትና የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ንብረቱ ከዘር የወረደ እርስት ስለሆነ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጡት ትርጓሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ እንደዚሁም ተጠሪው አውራሹ የሆነችው ወላጅ እናቱ የአናቷን የወ/ሮ ጀማነሽ አቦዬን ውርስ ሳትጠይቅ ያሳለፈችው ረጅም ጊዜ በተጠሪው ላይ የሚቆጠርበት መሆኑን ሣያገናዝብ ተጠሪው የይርጋ የጊዜ ገደቡ ሣያልፍ ነው ክስ የቀረበው በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ የተጠሪ የወራሽነት ጥያቄ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000(2) መሰረት በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ የቤቱን ባለቤትነት አስመልክቶ ያነሱትን ክርክር መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ከላይ በተገለፀው መንገድ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000(2) በተሣሣተ መንገድ በመተርጐም የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ የህግና የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማጽደቅ የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሄር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 255/1999 ጥር 22 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡